# ስልጣንን በኣመፅ

ከኣሉላ ዮሃንስ

የካቲት 21 2010

መቐለ

የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ማ ይሆናል የሚል የሰሞኑን ዋነኛ ኣጀንዳ ሆኖ በተለያዩ ሚድያዎችና ኣስተያየት ሰጪ ግለሰቦች እያነጋገረ ይገኛል። ስለሃገር መቆርቆርና ወደተሻለ ኣቅጣጫ እንድትመራ፣ ሰው በሰላም ወጥቶ እሚገባበትን እና በየተኛውም የሃገሪቱ ክፍል ሰርቶ ለመኖር የሚናፍቀው ህዝብ የዘወትር ምኞት ነው።

የኣስተያየት ሚዛኑ ብቻ ሳይሆን በግላጭ እንደነ ለማ ያሉ የድርጅት መሪዎች ግን በራሳቸው ግዜ የወሰኑና ያለምንም ጥርጥር የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን ቦታ ለመያዝ ውሳኔ ኣስተላልፈዋል፣ የሃገሪቱ ብሄራዊ ቋንቋም ኦሮምኛ እንዲሆን እንደሚታገሉ ወስነዋል። የተወካዮች ምክርቤት ኣባል ኣለመሆኑንና በዚሁም ምክንያት ለዚሁ ቦታ እንደማይሆንለት ሲነገረው ምክትሉን ትቶ ፀሃፊውን ወደሊቀመንበርነት ማምጣት መቻሉ በርግጠኝነት ሊቀመንበሩ ከኦሆዴድ እንደሆነ እየነገረን ነው። ይህንንም ለማሳካት በመንግስት ሚድያ የውሸት የኣብዲን የትግል ኣስተዋፅኦ በስፋት ተለፍፈዋል። ይህ ነገር ሆን ተብሎ ህዝቡን እና ሌሎች የኢህኣዴግ ድርጅት ኣባላትን ለማወናበድ የተዶለተ ሴራ ነው። የጥፋት እንጂነር የሃገሪቱ መሪ ሆነ ማለት ግን ሃገር ሳትሆን ገር ሆነች ማለት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ መሰረታዊ ለውጥ እናደርጋለን ብሎ ለሃገራችን ህዝብ ቃል የገባው ብኣዴንም የወር ዱለታው የኣባይ ውሃ በላው፣ ያለምንም መነካከት እንዳለ ወጥተዋል። ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂው ብኣዴን ነው ያለው ገዱ ተጠያቂነት ትርጉሙም የገባው ኣይመስልም ወይንም የህዝብ ንቀት በተጨባጭ እያረጋገጠ መሆኑን ማሳያ ነው።

ያም ሆነ ይህ ሃገሮቱን በመሪነት መሰየም ያለበት የመሰረተ ልማት ውድመትና የዘር ማጥፋት ዘመቻን በእንጅነርነት የመሩትንና ከኣስቸኳይ ግዜ ኣዋጅ ወዲህ እንኳን ከፍተኛ ተፅእኖ በመፍጠር ስልጣንን ለመቆናጠጥ ሲባል ነውጡን እንዲቀጥል እየመሩት ካሉት ሳይሆን በኣንፃራዊ መንገድ የተሻለ እንቅስቃሴ የነበራቸውን ድርጅት መሪ ነው ሊቀመንበር መሆን የሚገባው። ኣለበለዝያ ይህ ኣካሄድ እንደ ጥሩ የትግል ስልት ይወሰድና ስልጠን የፈለገ ድርጅት ነውጥና ኣመፅ በስትራተጂነት መጠቀምን ይያያዘዋል እናም ኣገራችን ሃገር ሳትሁን የከብቶች ገር ሆና ጠላቶቿዋ የሚመኙላት የደከመች ሃገር ትሆናለች ማለት ነው። በዚህ የምኞት ኣካኤድም የምትመራ ሃገርና የሚያስተዳድራት መሪ ይኖራል ማለት ዘበት ነው።